

# የፈርኦን ልጅ

- የሙሴ ወላጆች በግብፅ ውስጥ ባሪያዎች ነበሩ። በዚያ ይኖሩ የነበሩ እሥራኤላውያን ለአራት መቶ አመታት በባርነት ቀንበር ስር ነበሩ። ስለ ሙሴ እናት ስለ ዮካቤድ ታሪክ ስታነቡ ሙሴን ከወለደች በኋላ ለሶስት ወራት እንደደበቀችው ትረዳላችሁ። በዚያን ጊዜ በጭካኔ ከሚታወቀው ከግብፅ ንጉስ ከፈርኦን የሞት አዋጅ እንዲያመልጥ ለማድረግም ውሃ በማያሳልፍ ቅርጫት ውስጥ አድርጋ በአባይ ወንዝ ላይ ሕፃኑን ሙሴን ለቀቀችው። የአባይ ወንዝ ለግብፅ ሕይወት እጅግ በጣም አስፈላጊ ነው። ግብፃውያን የአባይ ወንዝ ልዩ የሆነ ኃይል እንዳለውም ያምናሉ።

- ቅርጫቱ ቢገለበጥና ልጁ ቢሰጥምስ? አዞዎች አግኝተው ቢበሉትስ? ወታደሮች ቢያገኙትስ? በዚህ ሁሉ ልጁ ምን ሊሆን እንደሚችል መገመት ትችላላችሁ?

- የሙሴ ታላቅ እህት ቅርጫቱ በሚሄድበት ሁሉ እየተከተለች የት እንደሚደርስ እያየች ነው። የፈርኦን ልጅ ሰውነቷን ልትታጠብ አባይ ወንዝ ዳር ላይ ነው ያለችው። ስሟን አናውቀውም። ምናልባትም ዮካቤድ ይህ አካባቢ በፈርኦን ልጅ በተደጋጋሚ እንደሚዘወተር ታውቃለች። የፈርኦን ልጅ አካባቢውን የምታዘወትርበት ዋነኛ ምክንያትም ሰውነቷን ለመታጠብ ነው። ታዲያ የሙሴ እናት የፈርኦን ልጅ ሕፃኑን በቅርጫት ላይ ስታየው እንደምትራራለትና እንደምታዝንለት ገምታለች።

❈ የግብፅ ልዕልትም ቅርጫቱ በአባይ ወንዝ ላይ በሸምበቆዎች መካከል ሲንሳፈፍ አየችው። ስለዚህም አገልጋይዋን ልካ ቅርጫቱን ስታስመጣው በውስጡ የሚያለቅስ ሕፃን አገኘች። ለመሆኑ በአጋጣሚ ይሆን እንዴ ቅርጫቱ ልዕልቲቱ ወዳለችበት ቦታ እየተንሳፈፈ የመጣው? አባቷ ፈርኦን የዕብራውያን ሕፃናት እንደተወለዱ እንዲገደሉ ያወጣውን አዋጅ በሚገባ ታውቃለች። የሕፃኑን ሕይወት ለማትረፍ ስትል ግን ከአባቱ መሻት ጋር በጣም ተቃራኒ የሆነ ነገር ማድረግ ነበረባት። ዕብራዊ በመሆኑ ብቻ ሊጠላ እንደሚችልም ታውቃለች።

❈ ማርያም ከተደበቀችበት ቦታ ወጣችና ልጁን ማጥባት የምትችል ሴት ማግኘት እንደምትችል ለልዕልቲቱ ነገረቻት። እናም የት የሄደች ይመስላችኋል? በርግጥም የሄደችው ወደእናቷ ወደ ዮካቤድ ነበር። ልዕልቲቱም ዮካቤድን ስታገኛት፣ "ይህንን ሕፃን ወስደሽ አጥቢው፤ ደመወዝሽን እከፍልሻለሁ፣" አለቻት። ዮካቤድ ልጇን ከማግኘቷም በላይ ደመዝተኛ ሆነች!

❈ ከእናቱ የሚለይበት ጊዜ ሲደርስም ከልዕልቲቱ ጋር እንዲኖር ወደ ቤተመንግስት መጣ። ልዕልቲቱም ሙሴ ብላ ጠራችው። ለዚህም ምክንያቱ ከውሃ ውስጥ ስላወጣችው ነበር። እንደልጇ አድርጋም አሳደገችው። በዚያን ጊዜ የነበረውን የመጨረሻውን የግብፅን ትምህርት ተምሮ አደገ። በሐዋርያት መፅሐፍ እንደምናነበውም

❈ የግብፃውያንን ጥበብ ሁሉ ተማረ፤ በቃልና በሥራም የበረታ ሆነ ይላል። ምናልባትም ስለታሪክ፣ ስለከዋክብት ምርምር፣ ስለእንስሳትና ስእፅዋት አጥንቶ ሊሆን ይችላል። የፈርኦን የልጅ ልጅ ነውና ያለጥርጥር ሄሮግሊፊክስ በመባል የሚታወቀውን የያኔውን የግብፃውያንን እጅ ፅሑፍ አንብቦ ይረዳል። አንዳንድ ምሁራን ሙሴ አልጋ ወራሽ ለመሆን ተቃርቦ እንደነበር ያምናሉ።

❈ ሙሴን ስላሳደገችው ልዕልት በመፅሐፍ ቅዱስ ውስጥ ብዙ የተፃፈና ብዙ የምናውቀው ነገር ባይኖርም በጣም ርህሩህና ደግ እንደነበረች እርግጠኛ መሆን ይቻላል። የአባቷን አዋጅ በመጣሷም እጅግ ደፋር ወይም ጀግና ነች ብሎ መናገር ይቻላል። ስለሙሴ በቤተ መንግስት ውስጥ ለነበሩ ሰዎች ምን ብላ ነግራቸው ይሆን? በአባይ ወንዝ ላይ እንዳገኘችው ተናግራ ይሆን? በሌሎቹ በቤተመንግስት ውስጥ በነበሩ ሕፃናትስ ተቀባይነት ይኖረው ይሆን? ሙሴ በቤተመንግስት ውስጥ ስላሳለፈው ቀሪ የእድገት ዘመኑ ብዙ የተፃፈ ነገር ስሌለለ እኛም በዚህ ረገድ ብዙ እውቀት አይኖረንም። ከዚህ በኋላ ስለሙሴ የምናውቀው ቢኖር አድጎ ትልቅ ሰው ስለመሆኑ ብቻ ነው። በዚህ ታሪክ ውስጥ የተጠቀሰችው ጀግና ሴት ሙሴ የእግዚአብሔርን አላማ እንዲያሳካ ትልቅ አስተዋፅኦ አድርጋለች። ከሞት አዳነችው። እንዲሁም ወላጅ እናቱ ከእርሷ ጋር በነበረበት ጊዜ ለወደፊት ሕይወቱ አዘጋጅታው ነበር። ቅንጦት የተሞላበትን የግብፅ ቤተ መንግስት ኑሮ ንቆ ወይንም ትቶ በመሄድ እስራኤላውያንን ከግብፅ ባርነት ነፃ አውጥቶ ወደ ተስፋይቱ ምድር ሊመራቸው ችሏል።

ስለፈርኦን ልጅ ታሪክ በዘፀአት ምዕራፍ 2 ውስጥ ማንበብ ይቻላል።